እንደ ኢትዩጵያ ባሉ ሕብረ ብሔራዊ በሆኑ ሀገራት የሕብረ ብሔራዊ ፌዴራላዊ ሥርዓት ግንባታ በዋናነት በተረዳነው ልክ በየጊዜው ሰርዓታዊ አካሄድ በያዘ መልኩ የፌዴራል ፎርሙላውን ይበልጥ እያጠራን በምንሄድበት አግባብ እየተገነባ የሚሄድ ፕሮጀክት ተደርጎ ሊታይ ይችላል።

አገራችን የፌዴራል ሥርዓት ዋና መነሻ ለረዥም ዘመን የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት የነበረውን የሕዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር፣ በሃገራቸው ጉዳይ ላይ እኩል የመሳተፍና የመወሰን ሥልጣን እንዲኖራቸውና ማንነታቸውና ቋንቋቸው እንዲከበር በሚል የተነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያለመ ነው።

ባለፉት ሦስት አስርት ዓመታት የሕዝቦችን ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ ከማሳደግ አንጻር የተሻለ ውጤት ቢመዘገብም የብሔር ማንነትን በማክበር የሕዝቦች የጋራ ማንነት ከመገንባት አንጻር የታየው ሰፊ ችግር የፌዴራል ሥርዓቱ ዋነኛ ተግዳሮት ተደርጎ ይወሰዳል።

በአገራችን ሁኔታ ግን በበርካታ የታሪክና ሌሎች ቁሳዊ ነገሮች ሊጨበጥ የሚችል እውነተኛ አብሮ የመኖር መስተጋብር መኖሩን ስለሚያመላክቱ፣ ለሀገረ መንግሥት ግንባታ የሚያስተሳስሩ እነዚህን የጋራ እሴቶችና ታሪኮች በአግባቡና ሚዛኑ ተጠብቆ መሰነድና ማስተማር የበለጠ ይጠቅማል።

በአንድ ፌዴራል ሥርዓት ውስጥ የተሳካ የአገር ግንባታና የተሳሰረ ማንነት ተገነባ የሚባለው፣ ሕዝቦች ራሳቸውን ማስተዳደራቸው አንድ ነገር ሆኖ፣ የሌሎችን ማንነት ማወቅና ማክበር፣ የዜግነት መብት ማወቅና ማክበር፣ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ጤነኛ የሆነ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት መፍጠርና የተሳሰረ/የተጋመደ አገራዊ አንድነት መፍጠር መቻልን ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ ግልጽ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች የባህል፣ የቋንቋ፣ የሚዲያ፣ የትምህርት፣ የታሪክ፣ የሕግ ሥርዓቱ፣ አርት፣ ሃውልቶች፣ ሳንቲሞችና ብሮች ላይ የሚቀመጡ ምልክቶች፣ ወዘተ… የዚህ ማራመጃ ዋና ማስፈጸሚያ ናቸው፡፡

*Websites* http://www.cityaddisababa.gov.et/

addisababacommunication@gmail.com

የአዲስ አበባ ከተማ ኮሙኒኬሽን ቢሮ
Addis Ababa City Communication

https://t.me/AAcommu

**‘ሕብረ ብሔራዊ አንድነታችን ለዘላቂ ሰላም’**

**17ኛው የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን**

**በአዲስ አበባ ኮሙኒኬሽን ቢሮ**

**የህዝብ ሚዲያ ግንኙነትና ይዘት ዘርፍ**

ህዳር 2015 ዓ.ም

ፌዴራሊዝም አንድ የፖለቲካ ሥርዓትን ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በሕዝቦች ፍላጎትና ምርጫ ለመገንባት የሚያስችል አስተሳሰብ ወይም አማራጭ ሀሳብ ነው። የፌዴራል ፖለቲካ ሥርዓት ደግሞ የፌዴራሊዝም አስተሳሰብ በተግባር የሚገለፅበት ተጨባጭ የፖለቲካ አደረጃጀት ነው። የፌዴራሊዝምን ፅንሰ ሀሳብ ተግባራዊ ለማድረግ የፌዴራል ፖለቲካ ሥርዓት አስፈላጊ ነው። ፌዴራሊዝም እንደ አስተሳሳብ ሁሌም ሊኖር ይችላል። የፌዴራል ሥርዓት ግን ያለ ፌዴራላዊ አስተሳሰብ እውን ማድረግ አዳጋች ነው፡፡

ፌዴራሊዝም እንደ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ በጋራ ለመቀጠል የወሰኑ ማኅበረሰቦች የራስ እና የጋራ ጉዳዮችን አጣምሮ ዴሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ ለማስተናገድ የሚያስችል ሥርዓትን መፍጠር ታሳቢ ያደረገ ፍልስፍና ነው፡፡ ፍልስፍናው ይህን አስተሳሰብ እና አስተሳሰቡ የሚገለፁባቸው እሴቶችን የመያዝ፣ የመደገፍ እና በተግባር የመግለፅ ጉዳዮችን የሚያካትት ነው። በፌዴራሊዝም ዙሪያ ሰፊ ምርምር ያካሄደው ኤላዘር (1987) እንደገለፀው ፌዴራሊዝም ሕዝቦች በእኩልነት መርህ፣ በመነጋገርና በመወያየት በቃል ኪዳን ማሳሪያነት የፖለቲካ ማኅበረሰብን የሚገነቡበት አማራጭ መንገድ ነው።

ፌዴራሊዝም የሰው ልጆች በእኩልነት መርህ አንድ ላይ በመሰባሰብ ሰፊና ጥልቀት ያለውን ውይይትና ድርድር በማድረግና ስምምነት ላይ በመድረስ ተፈጥሯዊ መብቶቻቸውን ለራሳቸው በማስቀረት በቃል ኪዳን ወይም ጥብቅ በሆነ ውል ማሰሪያነት ሰፊና ጠንካራ የጋራ ፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ማኅበረሰብ ለመገንባት የሚያስችል ሀሳብ ወይም አማራጭ መንገድ ነው። ውሉ የሕጋዊ ብቻ ሳይሆን የሞራላዊ ተጠያቂነትን የሚያስከትል በመሆኑ የቃልኪዳን ውሉ ከሌሎች ውሎች የተለየ ከመሆኑም በላይ ሞራላዊ መሠረት ያለው ትስስሩ ለቃልኪዳኑ መከበር ወሳኝ ተደርጎ ይታያል።

ፌዴራሊዝም የሚለው ጽንሰ ሃሳብ የቃሉ መነሻ የመጣው ፌዴራል ከሚለው ቃል ሲሆን ፌዴራል የሚለው ቃል ደግሞ የተወሰደው ፌዱስ/foedus/ ከተባለው የላቲን ቃል ነው። ትርጉሙም ቃልኪዳን/covenant/ ወይም ጥብቅ ውል/compact/ ማለት ነው (ኤላዘር 1987)። አስተሳሰቡም በመሠረታዊነት በቃልኪዳን ወይም ጥብቅ በሆነ ውል የተመሠረተ ሕብረት ወይም አጋርነትን የሚገልፅ ነው። የፌዴራል ፖለቲካ ሥርዓት ፍልስፍና ሕብረት የሚያደርጉ አካላት የራሳቸውን ህልውና/Integrity/ በጠበቀ ወይም ባከበረ መልኩ በጋራ ለመኖር የሚያስችል አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በቃልኪዳን ማሰሪያነት የሚገነባበት ነው።

ብሔር አንድ ማኅበረሰብ ነን የሚል እሳቤ ያላቸው፣ የሚጋሩት የጋራ ባህል‹ በግልጽ ከሚታወቅ መልካ ምድር ጋራ ራሳቸውን የሚያያይዙ፣ያለፈ የጋራ ጉዳይ እና የወደፊት የጋራ ፕሮጀክት አለን ብለው የሚያስቡና ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ያላቸው ሰዎች የተሰባሰቡበት ቡድን ነው።“ በመሆኑም በሀገራችን እንደዚህ ዓይነት እሳቤ ያላቸው ለብዙ አስርት ዓመታትም በዚህ መልክ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ያሏት ሀገር መሆኗ ይታወቃል።

በሕብረ ብሔራዊ ፌዴራላዊ ሥርዓት ብዝኃነትን ከሀገራዊ አንድነት ጋር ተመጋጋቢ አድርጎ ለማስኬድ አንዱ መንገድ ብዝኃ እና ተመጋጋቢ የሆኑ ማንነቶች እያበለፀጉ መሄድ መሆኑን የሌሎች ሕብረ ብሔራዊ የሆኑ ፌዴሬሽኖች ተሞክሮ ያሳያል።በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሥርዓቱ የተሻለ አማራጭ በመሆንና ሥርዓቱ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች እየፈታንባቸው በምንሄድባቸው መንገድ እንደ ሀገር ተቀራራቢ የሆነ አስተሳሰብ ይዘን መንቀሳቀስ የሚጠበቅብን ወቅት ላይ መሆኑን ማመላከት ተገቢ ይሆናል።